# በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ሴክተር

# የ10 ዓመት (2013-2022) መሪ የልማት ዕቅድ

ሚያዝያ, 2012 ዓ.ም.

**ሀዋሳ**

# መግቢያ

እንደ ሴንትራል ስታቲስቲካል ኤጀንሲ ትንበያ መሠረት የክልላችን ህዝብ ቁጥር እ.ኢ.አ. በ2012 3,438,052 ሚሊዮን እንዲሁም በ2022 ወደ 4,165,329 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ የከተሞችን የህዝብ ቁጥር ዕድገት በተመለከተ የክልላችን ከተሞች በመካከለኛ እድገት አማራጭ (Senario) በአማካይ 4.3 በመቶ እንደሚያድግና በ2022 በከተሞች የሚኖር የህዝብ ብዛት 2,982,188 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ዘላቂነት እና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለውን የመንቀሳቀስ ፍላጎት (Mobility Demand) ከወዲሁ ታሳቢ ያደረገ የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ግንባታ፣ የተቀናጀ፣ ፍትሃዊ ተደራሽነቱ የተረጋገጠ ትራስፖርት አገልግሎት ሊሸከም የሚችል የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅም መፍጠር ተገቢ በመሆኑ የክልሉ መንግስት ልማትን ለማፋጠንና ድህነትን ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ የሚያስችሉ አላማዎችን ያነገቡ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችንና የልማት መርሃ ግብሮችን እንደምተገብር ይታመናል፡፡

በዚህም መሠረት ከ2003-2007 እና ከ2008-2012 በጀት ዓመታት የዘለቀ ሁለት ተከታታይ በቀድሞ ዞናዊ የዓምስት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማዘጋጀት የክልላችንን ህዝቦች ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ባሻገር በ2017 አገራችንን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት አስተዋፅጸ ሊያበረክቱ የሚችሉ ግቦች ተጥለው ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በዚህ ረገድ የትራንስፖርት ዘርፍ በነዚህ በሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመናት /2003-2012/ በክልል ደረጃ ከተጣሉ ግቦች የድርሻውን በመውሰድ በትራንስፖርት ዘርፍ የተቀመጠውን የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አቅጣጫ ተከትሎ የመንገድና ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ፣የትራንስፖርት ኦፐሬሽን፣የመንገድ ትራፊክ ደህንነት፣ የአሽ/የተሽ ብቃት ማረጋገጥ እና በአጠቃላይ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ላይ ሰፊ ሥራዎች ሲተገበር ቆይቷል፡፡ አፈፃፀሙ ሲገመገም በአጠቃላይ በመንገድና ትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፉ የተያዙት ግቦች ተስፋ ሰጪ ቢሆንም ባለፉት አመታት የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ግንባታ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ተደራሽነትና ጥራት፣ የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲሁም የትራፊክ ደህንነትና ማኔጅመንት ስራዎች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ፍጥነት ልክ መጓዝ ባለመቻላቸው ትራንስፖርት አገልግሎቱ የጥራት፣ የብቃት፣ የተደራሽነትና የደህንነት ችግሮች አሁንም በስፋት የሚስተዋልበት ዘርፍ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ በአፈፃፀም ሂደት

የተለዩ ስኬትና ጉድለቶች ለቀጣይ ምዕራፍ ትምህርት የተወሰደበት ሲሆን በዘለቄታነት ዘመን ተሻጋሪ የላቀ የአፈፃፀም ውጤት ለማስመዝገብ፣ ለመካከለኛና አጭር ጊዜያቶች ዕቅድ መነሻና መሪ ሊሆን የሚችል የአስር አመት በፍኖተ ካርታነት የሚያግዝ መሪ ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊነቱ ታምኖበታል፡፡

በመሆኑም የትራንስፖርት ዘርፍ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2022) የተዘጋጀ ሲሆን የመሪ ዕቅዱ ትኩረት የተቋሙን የአደረጃጀት፣የአሰራርና የሰዉ ኃይል ጉድለቶችን በማስተካከልና የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት የዘርፉ ውጤታማነት ማሳደግ፣ የመንግሥታዊ ተቋማትንና የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፣ የትራንስፖርት መሠረተ ልማትን የማስፋፋትና የማጠናከር፣ የተቀናጀ የብዙሃን ትራንስፖርትን ተደራሽነት የማሳደግ፤ የመካከለኛ ትራንስፖርት የማስፋፋትና የማዘመን፣ የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት የማረጋገጥ እንዲሁም የትራፊክ ደህንነትን በከፍተኛ ደረጃ የማሻሻል እና የትራንስፖርት ዘርፍ ከአካባቢ ብክለት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ጫና የመቋቋም አቅም መፈጠር ይገኙበታል፡፡ የክልላችን የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ያስችል ዘንድ የዘርፉን ተጠሪ ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት በሰፊው ባሳተፈ መልኩ መሪ ዕቅዱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

# ክፍል 1

# 1. ያለፉት 10 ዓመታት አፈጻጸም

## 1.1 የትራንስርት ዘርፍ የነባራዊ ሁኔታ ግምገማ

የትራንስፖርት ዘርፍ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ሂደት የትራንስፖርት ዘርፉ ባለፉ ዓመታት ተግባራዊ በተደረጉ ሀገራዊ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች ያሳየው አፈፃፀም፣በአፈፃፀም ሂደት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችና መልካም አጋጣሚዎች መዳሰስ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም ባለፉት የልማት ዕቅዶች የትራንስፖርት ዘርፍ የነበረውን አፈፃፀም ግምገማ በትራንስፖርት መሰረተ ልማት፣በትራንስፖርት አገልግሎት፣በአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ፣በመንገድ ትራፊክ ደህንነት እና በመፈፀምና ማስፈጸም አቅም ግንባታ ዘርፎች ከፋፍሎ በሚከተለው መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል።

### 1.1.1 የአሽከሪካሪ ተሽከርካር ብቃት ማረጋገጥ

የአሽከሪካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ማውጣት፤አዲስ ለሚቋቋሙ ማሰልጠኛ ተቋማት ፈቃድ የመስጠት፣የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የሙያ ፈቃድ ዕድሳት ማድረግ፤የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋና ከብልሹ አሰራር የጸዳ እንዲሆን በካሜራ የታገዘ ፈተና የሚሰጥባቸዉ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ግንባታዎችን ማካሄድ።

የሽከርካሪዎችን ቴክኒክ ምርመራ በማካሄድ የቴክኒክ ጉድለት ያለባቸውን ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በመከታተል ማገድ፤ ለባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉ ሠሌዳዎችን፣ሊብሬ፣ ቦሎዎች ማሳተም፣ ማሰራጨት፤የተሽከርካሪ መጠገኛ ጋራዥ ብቃት ማረጋገጥ ፤ፈቃድ መስጠት፣ ማደስና መከታተል፤ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፍቃድ መስጠትና ማደስ፤ መመሪያዎችን ማውጣት። የአሽከርካሪዎችን ክህሎት፣ እውቀትና ስነምግባር ከማሳደግ አንጻር 90 አዲስ ብቃታቸው የተረጋገጠ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን ለማቋቋም ታቅዶ 89 በማቋቋም አፈጻጸሙ 99% ሲሆን 186,250 አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 198094 በመስጠት አፈጻጸሙ 106%፤80,000 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች ለፎርጀሪ

እንዳይገለጡ ላምኔትድ ለማድረግ ታቅዶ 122,123 መንጃፍቃድ ላሚኔት የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም 152 % ነው፡፡

በመገንባት ላይ ያለው አዲስ የአሽከርካሪዎች የተግባር ሥልጠናና ምዘና ማዕከል /ትራፊክ ኮምኘሌክስ/ ግንባታ ለማካሄድ ታቅዶ ሀዋሳ እየተገነባ የሚገኘው የትራፊክ ኮምፕሌክስ ግምባታው በዲዛይኑና ውሌታው መሠረት ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ቢሆን በዲዛይን ወቅት መካተት ያለባቸውና ያልተካተቱ ሥራዎች ለአብነትም የዳገት ቁልቁለት መፈተኛና ማሰልጠኛ መንገዶች፣ የCCTV ካሜራ የመዘርጋትና የውስጥ ለውስጥ አስፋልት ስራዎች ባለመካተታቸው ወደሥራ ማስገባ አለመቻል፤ በዲዛይን ላይ ያልተካተቱ ችግሮችና የቦታው ስፋት ከዓለማቀፍ ደረጃ አንፃር በቂ ባለመሆና የተቋራጭ ድርጅቶች በውሌታው መሠረት ባለመሥራታቸው ውለታው ተቋርጠዋል፡፡

በየዓመቱ ምዘና ያለፉ ሰልጣኞች /አሽከርካሪዎች/ በመቶኛ 100% ለማሳለፍ ታቅዶ በአሁኑ ሰዓት የተግባርም ሆነ የንድፈ ሀሳብ ምዘና ለመውሰድ ከተቀመጡት ሰልጣኞች ስንት ተቀምጠው ስንት አልፎ ነው ውስጥ 75% ማሳለፍ ተችሏል፡፡ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ከማሳደግ አንጻር 289,300 ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 280,325 በማከናወን አፈጻጸሙ 97%፣ 92,150 ድንገተኛ የተሽከርካሪ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 50,902 አፈጻጸሙ 55%፣44 የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ለማቋቋም ታቅዶ 4 በማቋቋም አፈጻጸሙ 9% እና 350 የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ለማቋቋም ታቅዶ 162 ተቋማት በማቋቋም አፈጻጸሙ 46% ሲሆን ከተቀመጠው ግብ አንጻር ዝቅተኛ አፈፃፀም መሆኑ ተገምግሟል፡፡

## 1.1.2 የህዝብ ትራንስፖርት አገ/አደ/ብቃ/ማረ ሥራ አፈጻጸም

በክልሉ እስከ መናኸሪያ ለሚገኙ ፈጻሚዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በጥናት በተለዩ ርዕሶች ላይ የአቅም ግንባት ስልጠና መስጠት፤የንግድ የህዝብ ማመላለሻ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ድርጅቶችና ማህበራት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል እንድሁም ለሚሰጡት አገልግሎት ታሪፍ ማዘጋጀት፤ለህዝብ የንግድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪዎች ደረጃ መመዘኛ /እስፔስፊኬሽን/ ማውጣትና መከታተል፤የሕዝብ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች ማህበራት የሚያቀርቡትን የስምሪት ፕሮግራም ማጽደቅና ስምሪት መስጠት፤አዳዲስ የስምሪት መስመር ማጥናትና መክፈት፤የአጎራባች ክልሎችን የሚያገናኝ የስምሪት መስመሮች ማጥናትና መክፈት፤በገበያ ስርዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤የህዝብ የንግድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩት የተሽከርካሪ ባለንብረቶችና ድርጅቶች

የሚያቋቁሟቸውን ማህበራት ፍቃድ መስጠት፣ማደስና መከታተል፣የንግድ የህዝብ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎችን ደረጃ መስጠት፣በክልሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ባልሆኑባቸው ቦታዎች በፍራንቻይዝ አግባብ ማሰራት፣የመካከለኛ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያዎች ናሙና ምርት እንዲስፋፋ ማበረታታት፤ አማራጭ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋት፣የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት ፎርማታዎችን ማልማት፣ሼዶችን መገንባት፣ የከተማ ታክሲ መናኸሪያ መለየትና ታሪፍ ማዘጋጀት፣የህዝብ ትራንፖርት መናኸሪያዎችን መገንባት እና ማህበራትን ፍቃድ መስጠትና ማደስ፣የትራንስፖርት አገልግሎች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ለትራንስፖርት አገልግሎቶች የሚውሉ የህትመት ውጤቶች ማሳተምና ማሰራጨት፡፡

በመሆኑም የህዝብ ትራንስፖርት የሚሰጥባቸዉ የስምሪት መስመሮች 2019 ለማከናወን ታቅዶ 1878 ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 93%፣ዞኖችን ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚያገናኙ 136 የስምሪት መስመር ለመክፈት ታቅዶ 135 የስምሪት መስመሮችን መክፍት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 99%፣በትራንስፖርት የተጓጓዘ ተሳፋሪ ቁጥር 51,593,887 ለማድረስ ታቅዶ 90,234,981 ለማድረስ ተችሏል፡፡ የትራንስፖርት አገልግሎቶች አደረጃጀትና ስምሪትን ከማሳደግ አንጻር 89 አዲስ መናኸሪያ ለመገንባት ታቅዶ 104 በመገንባት አፈጻጸሙ 117%፣የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራትን በማደረጀት 64 ለማድረስ ታቅዶ 62 በማደራጀት አፈጻጸሙ 97%፣ 62 የከተማ ታክሲ ማህበር ለማደራጀት ታቅዶ 77 በማደራጀት አፈጻጸሙ 124%፣የ184 መናኸሪያዎች ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ የ89 መናኸሪያዎች ደረጃ በማሻሻል አፈጻጸሙ 48.3% ነው፡ የትራንስፖርት ሽፋንን ለማሳደግ አማራጭ የከተማ ትራንስፖርት ከማስፋፋት አንጻር 5 አማራጮች /ቀላል ባቡር፣አዉቶብስ፣ላዳ፣ሚኒባስ፣ እና ባጃጅ ታክሲ/ ታቅዶ 3ቱን በማስፋፋት አፈጻጸሙ 60% ማድረስ ተችሏል፡፡ 36 የውሃ ላይ ትራንስፖርት ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ 14 በመስጠት አፈጻጸሙ 39% ሲሆን መካከለኛ ትራንስፖርት መገልገያ ጥናት/IMT/ 25 ዓይነት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ 4ቱ በጥናቱ መሰረት ተጠናቅቆ ናሙና የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙ 16% ነው፡፡

## 1.1.3 ጭነት ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጥ አፈጻጸም

የጭነት ትራንስፖርት ተግባርን የማስፋፋት ሥራ እየተሰራ ሲሆን በዚህም የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን የማደራጀት፣የግል ኦፐሬተሮችንና ኩባንያዎችን የማደራጀት፣የጭነት ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን የማስገንባትና የማስከለል፣የጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን ወደ ክልሉ ሰሌዳ እንዲቀይሩ ማድረግ፤ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መረጃ በመጫን ችሎታቸውና በአገልግሎት ዘመናቸው የማደራጀት ሥራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በክልሉ የሚገኙ የጭነት

ተሽከርካሪዎች መረጃ በመጫን ችሎታ በደረጃ እና በአገልግሎት ዘመን ማደራጀት (incod) ለማድረግ 1000 ለማደራጀት ታቅዶ 1500 ማደራጀት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 150% ነው፡፡ 43 አዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን ለማደራጀት ታቅዶ 40 ማህበራትን ማደራጀት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 93% ነው፡፡ ለጭነት ተሽከርካሪዎች መናኸሪያ እንዲገነባ ለማድረግ 16 ታቅዶ በ3 ከተሞች ላይ ግንባታው እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## 1.1.4 የመንገድ ደህንንት ብቃት ማረጋገጫ ሥራዎች አፈጻጸም

ለመንገድ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍልና ባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ በመፍጠርና የትራፊክ ህግ እንድከበር ማድረግ፤በመገናኛ ብዙሀንና በት/ቤቶች እንድሁም በማህበረሰቡ ዘንድ የህዝብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በስፋት እንዲሰጥ በማድረግ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ይደርስ የነበረውን የሞት አደጋ መጠን እንዲቀንስ ለማድረግ ነው፡፡ በመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ የመንገድ የትራፊክ ደህንነት ሥርዓት በመገንባት የመንገድ ደህንነት ከማረጋገጥ አኳያ ለትራንስፖርት ከተዘረጉ መስመሮች ውስጥ አደገኛ የሆኑ ቦታዎችን መለየት፤የትራፊክ አደጋ ተጠቂ ዜጎች በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ እና በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሥራ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ማበረታታት፤በመንገዶች ላይ የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት እንዲኖር አደጋን ለመቀነስ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በት/ቤትና በመንገድ ዳር ቀበሌዎች መሥራት፤ የመንገድ ደህንነት ኮሚቴዎችን የማደራጀትና  የማጠናከር ሥራ እንድሁም የተማሪ ትራፊኮች የማሰልጠን ሥራ እንድሰራ ተደርጓል፡፡ ከባለድርሻ አካለት ጋር በመሆን የቁጥጥር ስራዎችን በመስራት ከሞላ-ጎደል የህብረተሰቡ ጉዞ ሰላማዊ እንድሆን የማድረግ ሥራ በስፋት ተሰርቷል፡፡ በክልሉ አስፋልት ገብ በሆኑ መንገዶች ላይ የእግረኛ ማቋረጫ ዜብራ በመቀባት ህብረተሰቡ እንዲጠቀም የማድረግና የመንገድ ዳር ምልክቶችን የመትከል ሥራ እንዱሁም በእንስሳት ለሚሳቡ ጋሪዎች  አንፀባራቂ ምልክት የማሰራጨት ሥራ ተሰርቷል፡፡

የመንገድ ትራፊክ አደጋ ከመቀነስ አንጻር በየዓመቱ በ10% የመንገድ ትራፊክ አደጋ በመቀነስ ከመነሻው 1249 የነበረውን የአጠቃላይ አደጋ መጠን ወደ 738 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ  ወደ 1320 ከፍ በማለትና እንዲሁም በየዓመቱ በ10% የህይወት ጉዳት /ሞት/ በመቀነስ ከመነሻው 371 የነበረውን የሞት አደጋ መጠን ወደ 203 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 594  በመጨመሩ በተያዘው GTP እቅድ መሠረት አለመሳካቱን ያመለክታል፡፡ በየዓመቱ 10% የንብረት ጉዳት /በገንዘብ/ ስተመን በመቀነስ ከመነሻው **18,449,641** የነበረውን የንብረት ጉዳት ወደ 10,905,460  ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 13,890,236 በመሆን፣ የመንገድ አጠቃቀም ትምህርት ያገኘ ህብረተሰብ ቁጥር

በማሳደግ ለ69,114,916 ህዝብ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታቅዶ ለ98,208,855 ህብረሰብ ግንዛቤ በማስጨበጥ አፈጻጸሙ 142% ሆኗል፡፡

አዲስ የመንገድ ደህንነት የቀበሌ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም 4112 ታቅዶ 5750 በማቋቋም አፈጻጸሙ 140% መሆኑ፤በየዓመቱ አዲስ የመንገድ ደህንነት ክበባት ለማቋቋም 6331 ታቅዶ 6428 በማቋቋም አፈጻጸሙ 102%፣የእግረኛ ማቋረጫ 2500 ዜብራ ለመስራት ታቅዶ 6809 ቦታዎች ላይ የዜብራ ቀብ በመሰራቱ አፈፃፀሙ 272% ነው፡፡ 3992 የመንገድ ዳር ገላጭ ምልክቶች ለመስራት ታቅዶ 4659 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 117% ሲሆን 6077 አለምአቀፍ የመንገድ ዳር ምልክቶች እንዲዘጋጁና እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 7569 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 125% ነው፡፡

## 2. የዘርፉ ውጫዊ እና ውስጣዊ ግምገማ (SWOT Analysis)

### 2.1 ጠንካራ ጎኖች

- የ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ለትራንስፖርቱ ዘርፍ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 161/2008 መሰረት ትራንስፖርትና መንገድ ልማት በቢሮ ደረጃ እንዲቋቋም መደረጉ፡
- የትራንስፖርት ልማት ስትራቴጂና ፕሮግራም ተነድፎ ወደ ተግባር መገባት መቻሉ፣ ከስትራቴጂና ፕሮግራሙ የመነጩ የውስጥ ደንቦች፣መመሪያዎችና የተግባር አፈጻጸም ማኑዋሎች መዘጋጀታቸዉ፣
- በትራንስፖርት ዘርፍ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም የማሳደግ ስራዎች መከናወናቸው፤
- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ደብተር ለፎርጀሪ እንዳይጋለጥ ላሚኔት መደረግ መጀመሩ
- በመንግስት ደረጃ የትራፊክ አደጋ ልዩ ትኩረት መሰጠቱ፣
- የማሰልጠኛ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ፤
- የመካከለኛ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያዎች ናሙና ምርት መመረቱ፣
- የግል ባለሃብቶች በዘርፉ ያላቸው ተሳትፎ  እያደገ መምጣቱ፣

- የመንገድ ደህንነት ትምህርት በመደበኛና ኢ-መደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት ተካትቶ ጅምር ሥራ መኖሩ

- ከመገናኛ ብዙኃን እና ከአከባቢ ሬድዮ ጣቢያዎች ጋር በመተባበር ትራንስፖረትን አስመልከቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች በስፋት መተላለፍ

- የመንገድ ላይ የትራፊክ ቁጥጥር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ(sms) እንዲታገዝ መደረጉ

- በመናኸሪያ ውስጥ የስምሪት መከታተያና መቆጣጠርያ መዝገብ መኖሩ

- የጭነት ትራንስፖርት እራሱን ችሎ ዘርፉ እንዲመራ መደረጉ

## 2.2 ችግሮች

- በክልል ደረጃ አንፃራዊ የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ አለመኖሩ በትራንስፖርት ስምሪቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣
- የግንባታ እና የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረትና የዋጋ መናር በመሰረተ ልማት ግንባታው እና ትራንስፖርት አቅርቦቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣
- በዘርፉ የሚፈለገው የሰለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት መኖሩ፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በተገቢው ደረጃ ተቀናጅቶ የመስራት ውስንነት መኖር፣
- በሚሰጡ አገልግሎቶች ሕብረተሰቡን አለማርካትና የተገልጋይ አስተያየት እንደ ግብዓት ወስዶ አለመጠቀም፣
- ዘርፉ ለሙስና፣ ህገ ወጥ እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ መሆኑ፣
- ትራንስፖርት ዘርፉን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያለመተሳሰሩ
- ጠንካራና ተከታታይ የሆነ የድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙን በመርሃ ግብሩ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የመገምገም ዉስንነት፣
- የመናኸሪዎች መሰረተ-ልማት ደረጃዉን የጠበቀ አለመሆኑ፣
- የትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም፣
- የመንገድ ትራፊክ አደጋው እየጨመረና አሁንም ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ መሆኑ፣
- የጭነት ትራንስፖርት የመናኸሪያ አቅርቦት ያለመኖር፣
- ሀገራዊ ወጥ ሰሌዳ አለመኖሩ፣
- የጭነት ትራንስፖርት አደረጃጀት ሀገራዊ ወጥ አለመሆኑ፣
- የአሽከርካሪዎች ዕውቀትና ስነምግባር ችግር መኖር፣

- ጋራዦች በኢንዳስትሪ ዞን አለመደራጀታቸው ለአካባቢ ብክለት አባባሽ ምክንያት ሆነው መገኘታቸው፣
- የአሽከርካሪ መመርመሪያ ተቋማት ከብልሹ አሰራር የፀዱ አለመሆናቸውና ተገቢውን አገልግሎት አለመስጠት፣
- የትራፊክ ኮምፕሌክስ ግንባታዎች መዘግየት
- የመንገድ መሠረተ ልማት ችግር ለአደጋ መንስኤ መሆን
- የመንገዶች ጥገና በወቅቱ አለመደረግ
- የካፒታል ፕሮጀክቶችን የመፈፀም አቅምና ዲዛይን ችግር መኖር

## 2.3 መልካም ዕድሎች

በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ለተቋሙ የልማት እንቅስቃሴ የሚከተሉት ምቹ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

- ለትራንስፖርት ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱ፣
- የሕብረተሰቡ እና የባለሃብቱ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መምጣቱ፣
- ከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና በፈጣን የሕዝብ ዕድገት ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የጭነትና የሕዝብ ትራንስፖርት ፍላጎት መኖሩ፣
- የከተሞች መስፋፋት እና የህብረተሰቡ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ  እያደገ መምጣት፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ ምቹ የሆኑና ወቅቱን የሚያንጸባርቁ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች መነደፋቸው፣
- የህግ ማዕቀፎች መዘርጋታቸው፣
- በፌደራል መንግስትና በክልሉ መንግስት ለከተማ ውስጥና ለአውራ ጎዳና መንገዶች እና የቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ ፕሮግራም ከፍተኛ የሆነ የመንገድ መሰረተ ልማት እየተዘረጋ መሆኑ፡፡

## 2.4 ስጋቶች

የተቋሙ የወደፊት አስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ሲተገበር አደናቃፊ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ የሚከተሉት ስጋቶች ተለይተዋል፡፡

- በነፃ ገበያ መርህ መሰረት የሚመራ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ጥራት ያለውና ተደራሽ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የትራንስፖርት ማህበራትና ኩባንያዎች አለመኖር፣

- በአገር አቀፍ ደረጃ አንፃራዊ የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ አለመኖሩ በትራንስፖርት ስምሪቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በተገቢው ደረጃ ተቀናጅቶ የመስራት ባህሉ የዳበረ አለመሆን፣
- በዘርፉ የሚፈለገው የሰለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት መኖሩ፣
- የግንባታ እና የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረትና የዋጋ መናር በመሰረተ ልማት ግንባታው እና ትራንስፖርት አቅርቦቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣
- ብልሹ አሰራርና ኪራይ ሰብሳቢነት አስጊ ደረጃ መድረሱ፣
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በሚፈለገው መጠን አለመዳረስ፣
- የአካባቢ ብክለት

## 2.5 ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆኑ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች

ይህ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ለዘርፉ ታሳቢ የተደረጉ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች፡-

- በከፍል የዘርፉ እውቀት፣ክህሎት እና የረጅም ዘመን የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችና አመራሮች፣
- የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች፣
- ተሽከርካሪ ጥገና ጋራዦች፤የህዝብና የጭነት ትራ/ማህበራትና የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋማት፤
- የመ/ቤቱ ህንጻዎችና ተሽከርካሪዎች
- ከመላጎደል ለሁሉም ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች ኮምፒዩተር አላቸው
- የተሟላ የኢንተርኔት መሥመር

# ክፍል 2

# የ2013-2022 የትራንስፖርት ዘርፍ የልማት ዕቅድ

## 2.1 የልማት ዕቅዱ ራዕይ፣ተልዕኮ፣ዓላማዎች፣ግቦችና ማስፈጸሚያ ስልቶች

### 2.1.1 ራዕይ

"በ2022 ዘመናዊ፤ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ህጋዊና ፍትሀዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሁሉም የክልሉ ህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ሆኖ ማየት"

### 2.1.2 ተልዕኮ

"በትራንስፖርት ዘርፍ የሬጉላቶሪና ኢንፎርመንት አቅም በማሳደግ የባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና በመደገፍ የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በሥራ ላይ በማዋል ቀልጣፋ፣ኢኮኖሚያዊ፣ደህንነቱንና ምቾቱ የተጠበቀና ከክልሎች ጋር የተሳሰረ የመንገድ አውታርና ዘመናዊ ትራንስፖርት አገልግሎት ስርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡ ፍላጎት ማሟላትና ዘርፉ ለክልሉ ዕድገት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲያበረክት ማድረግ"

### 2.1.3.መነሻዎች

- ያለፈው አስር ዓመት አፈጻጸም
- በክልሉ እያደገ የመጣውንና ወደፊትም ሊያድግ የሚችለውን ኢኮኖሚ መሸከም የሚችል የትራንስፖርት ሥርዓት መገንባት፣
- በዘርፉ ያለውን ሀብት (Resource) በአግባቡ በመጠቀም ምቹ፣ቀልጣፋና፣ተጠያቂነት ያለበት አሰራርን በማስፈንና ችግሮችን በመቅረፍ ውጤታማ የሥራ አፈጻጸም እንዲኖር ማድረግ፣
- የትራንስፖርት ዘርፉን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አያያዝ እንዲኖር ማስቻል፣
- የትራንስፖርት ዘርፉን የማስፈጸም አቅምን በማሳደግ የተሻለ ደረጃ ማድረስ፣
- የከተማ ትራንስፖርት አሰራርን ማዘመንና አማራጭ ትራንስፖርትን ማስፋፋት፣
- በገጠር ቀበሌዎች የመካካለኛ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያዎችን ማስፋፋትና ማዘመን፣

### 2.1.4 የትኩረት አቅጣጫ

- የማስፈፀም አቅም በማሳደግ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ አገልግሎት መስጠት፣
- የትራንስፖርት መሰረተ ልማት አቅርቦቱን ማሻሻል
- ደህንነቱ የተጠበቀና በዘመናዊ ተክኖሎጂ የታገዘ የትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥን ማስፈን፣
- የህብረተሰቡን ተሳትፎ  እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ

### 2.1.6 ዓላማዎች/ግቦች/

- የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤
- የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣
- የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፣
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሰረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣
- የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት የዘርፉ ውጤታማነትን ማሳደግ

## 2.3 የትራንስፖርት ዘርፍ የአስር ዓመት የልማት ግቦች

### ግብ 1፡ የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ

- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና መስጫ /ትራፊክ ኮምፕሌክስ/ በ 2 ዞኖች ላይ መገንባት፤

- በ በሁሉም ዞኖች ውስጥ የሚገኙ ጋራዦች በጥገና ወቅት የሚወጣውን አከባቢ በካይ ጋዝ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመከላከል እንዲቻል ጋራዦችን በኢንደስትሪ ዞን ማደራጀት

- የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን በመገንባት አሁን ከነበረበት 27 ወደ 50 ማድረስ፣
- 4 የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን  ከደረጃ 2 ወደ ደረጃ 1 ማሻሻል
- 22 የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 2 በማሻሻል ወደ 50 ማድረስ
- በከተሞች 40 የከተማ ታክሲ መናኸሪያዎች መለየትና 5 መገንባት፣

- በ 36 ከተሞች የስምሪት መስመሮች ላይ የተሳፋሪ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎችን በመለየት ከ_____ወደ___ማድረስ፣
- በከተሞች ውስጥ የስምሪት መስመሮች ላይ 40 ሼዶችን መገንባት
- 20 የመኪና ማቆሚያ ፓርኪንግ መገንባት
- 1 ቀላል የከተማ ባቡር መገንባት
- በ 4 ከተሞች ላያ የሳይክል መንገድ ለይቶ ተግባራዊ ማድረግ
- የጭነት ትራንስፖርት መናኸሪያ ግንባታ አሁን ካለበት ከ 0 ወደ 10 ማድረስ
- የመንገድ ጥናትና ዲዛይን አሁን ካለበት__________ ኪ.ሜ ወደ_________ ኪ.ሜ ለማሳደግ በመደበኛው መንገድ ግንባታ ፕሮግራም አሁን ካለበት_________ ኪ.ሜ ወደ_________ ኪ.ሜ ፣በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም አሁን ካለበት_______ ኪ.ሜ ወደ_________ ኪ.ሜ፣
- የድልድይ ጥናትና ዲዛይን አሁን ካለበት ________ ወደ________ ለማሳደግ በመደበኛው ፕሮግራም__________ድልድዮች እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ________ ወደ________ ማሳደግ፣
- የመንገድ ግንባታ አሁን ካለበት___________ኪ.ሜ ወደ__________ ኪ.ሜ ለማሳደግ በመደበኛው ፕሮግራም አሁን ካለበት______ ኪ.ሜ ወደ_________ኪ.ሜ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም አሁን ካለበት_________ ኪ.ሜ ወደ_________ ኪ.ሜ ማሳደግ፣
- የመንገድ ደረጃን ከማሻሻል አንፃር በመደበኛው ፕሮግራም አሁን ካለበት___________ኪ.ሜ ወደ_________ኪ.ሜ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ______ኪ.ሜ. ማሳደግ ነው፣
- የድልድይ ግንባታ አሁን ካለበት______ወደ_______ለማድረስ በመደበኛው ፕሮግራም ከ______ወደ________ማድረስና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ______ ወደ________ ማድረስ፣
- የመንገድ ጥገናና ደህንነት አሁን ካለበት__________ ኪ.ሜ ወደ_________ ኪ.ሜ ለማሳደግ በመደበኛ ፕሮግራም ከ____________ኪ.ሜ ወደ__________ኪ.ሜ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም________ ኪ.ሜ መጠገን.

ግብ 2: የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፣

- 6564 ቦሎዎችን በጥራዝ ማሳተምና ማሰራጨት፤100,000 ሰሌዳዎችን ማሳተምና ማሰራጨት፤100,000 የተሽከርካሪ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ ማሳተምና ማሰራጨት፤
- 200,000 የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤
- 60,000 ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ላምኔትድ ማድረግና ማሰራጨት፤
- ክልሉን ከአጎራባች ክልሎች የሚያገናኘውን የስምሪት መስመር ቁጥር ከ_______ ወደ_______ማሳደግ:
- የከተማና የገጠር የስምሪት መስመሮችን አሁን ከነበረበት________ ወደ_________ማድረስ
- በክልሉ አሁን ላሉና ወደ ፊት ለሚከፈቱ የትራንስፖርት ስምሪት መስመሮች የጉዞ መስመሮችን የሚያሳይ 1 ካርታ /Route map/ ማዘጋጀት፣
- በክልሉ አሁን ያሉትን የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ከ_____ወደ_______ ማድረስ፣
- አሁን ያሉትን የህዝብ ትራንስፖርት ልዩ ባስ አክሲዮን ማህበርን በማደራጀት ከ 0 ወደ 3 ማድረስ
- የተጓጓዘ ተሳፋሪ ቁጥር ከ_________ወደ_______________ ማድረስ፣
- የሥምሪት ምልልስ ከ ___________ወደ_______________ በማድረስ የኪሎ ሜትር ሽፋን ____________ ወደ______________ማድረስ
- የተጓጓዘ የከተማ ታክሲ ተሳፋሪ ቁጥር ከ--------ወደ---- ማድረስ
- በክልሉ የህዝብ የንግድ ማመላለሻ የሚሰጡ ማህበራትን ቁጥር ከ_______ወደ_________ ማድረስ፣
- የመካከለኛ የህዝብ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያ ማስፋፋትን አሁን ከነበረበት 0 ወደ 4 ናሙና ምርት ማድረስ
- የከተማ ብዙሃን ትራንስፖርት የማጓጓዝ ድርሻ ከ 2% ወደ 50% ማድረስ
- የከተማ ታክሲ ማህበራትን በማደራጀት ከነበረበት 4 ወደ 30 ማድረስ
- አማራጭ የከተማ ትራንስፖርትን ለማስፋፋት በ10 ከተሞች የከተማ አውቶቢስ፣በ20 ከተሞች ሚኒ ባስ እና በ1 ከተማ ቀላል ባቡር ማስፋፋት

- የማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት በኤሌክትሪክ እና በታዳሽ ሀይል ድብልቅ የሚሰሩ አውቶብሶች 10 ወደ ሥራ ማስገባት
- በተለየ መስመር የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ተግባራዊ የተደረገባቸው ከ 50 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች ብዛት ወደ 8 ማድረስ
- በወንዞቸና ሀይቆች ላይ  የሚሰሩ ባለሞተር ጀልባ ኦፕሬተሮችን አሁን ካለበት________ ወደ________ ማድረስ
- የፐብሊክ ሰርቪስ ትራስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት ወደ 10,000 ማድረስ
- የፐብሊክ ሰርቪስ አውቶቡስ አቅርቦት ብዛት ከ 2 ወደ 20 ማድረስ
- የገጠር መንገዶች መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋን በመቶኛ ከ 50 ወደ 100 ማድረስ
- አዳዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን ከነበረበት 3 ወደ 10 ማድረስ
- በጭነት ትራንስፖርት በድርጅት ወይም በኩባንያ ለሚደራጁ ባለሀብቶች የደረጃ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ 0 ከነበረበት ወደ 5 ማሳደግ
- የጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች የብቃት ባረጋገጫ ደረጃ ________ ከነበረበት____ ማድረስ
- በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ የግል ኦፕሬተሮች አደረጃጀት በጭነት አይነት /Specialization/ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን___________ ከነበረበት_________ማድረስ፣
- የፌደራል የወጡ ህጎችና ደንቦችን ወደ ክልሉ ነዋራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አምስት ሰንድ መቀየር አምስት ሰነድ ማዘጋጀት፡፡

**ግብ 3፡ የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ**

- በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት የሚሰጡ ማሰልጠኛ ተቋማትን ድርሻ ከ 65 ወደ 100 ማድረስ
- በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የሚሰጡ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ድርሻ በመቶኛ ከ25 ወደ 100 ማድረስ
- 20 የነበረውን የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን ቁጥር ወደ 30 ማድረስ
- አለም አቀፍ ደረጃ የጠበቁ የአሽከርካሪ ሞዴል ማሰልጠኛ ተቋማት ብዛት ወደ 10 ማሳደግ፣

- በሲሙሌተር የተደገፈ የአሽከርካሪዎች እና የቴክኒሽያኖች የተግባር ስልጠና በመቶኛ 6 ከነበረበት 100 ማድረስ
- 1 የነበረውን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ቁጥር ወደ 4 ማድረስ
- ________የነበረውን የተሽከርካሪ ጥገና መስጫ ጋራዦች ቁጥር ወደ______ ማድረስ
- ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ በዓመት 16000 ከነበረበት ወደ______ ማድረስ፤
- ብቃታቸው የተረጋገጠ ተሽከርካሪዎችን መመዝገብ 25000 ከነበረበት ወደ_________ ማድረስ
- የተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ_________ከነበረበት_________ ማድረስ
- ብቃታቸው የተረጋገጠ አሽከርካሪዎች ከ 35000 ወደ 70000 ማድረስ
- 1320 የትራፊክ አደጋ አሁን ከነበረበት በ5% በየዓመቱ በመቀነስ በ2022 ወደ 789 ማድረስ፤
- ሞት የሚያስከትል አደጋ ከ594 በ5% በመቀነስ ወደ 355 ማድረስ
- የንብረት ዉድመት ከብር 30,600,469 በ5% በመቀነስ ወደ ብር 18,321,632 ማድረስ
- በሰው ህይወት ላይ በአስር ሺህ ተሽከርካሪ ይደርስ የነበረውን 48 ሞት ወደ 10 ማድረስ
- የደህንነት ቀበቶ (safety belt) ገጥመዉ ተግባራዊ ያደረጉ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር በየአመቱ በ30% በማሳደግ 100% ማድረስ
- የፍጥነት መገደቢያና GPS መሳሪያ የገጠሙ የንግድ ተሽከርካሪዎች ቁጥር በየአመቱ በ20% በማሳደግ 100% ማድረስ
- የትራፊክ አደጋ በተከታታይ የሚደርስባቸዉን ቦታዎችን በመለየት ጠቋሚ ምልክቶችን (1500 አለም አቀፍ ምልክቶችን፣100 የማስጠንቀቂያ ማብራት፣4000 ገላጭ ጽሁፎችን፣ 8000 የእግረኛ ማቋረጫ (ዜብራ) እና 400 የፍጥነት መገደቢያ) ማኖር
- የአህያ ወይም የፈረስ ጋሪ አንፀባራቂ አሁን ከነበረበት 26000 ወደ 76,000 ማድረስ
- የትራንስፖርት ዘርፍ ህጎች አፈፃፀም በመቶኛ ከ50% ወደ 100% ማድረስ
- የተሽከረርካሪዎች የኦፕሬተር ደረጃ ብቃት ማረጋገጫ ከ460 ወደ 4600 ማድረስ

## ግብ 4፡ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሰረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ

- 2,000,000 ችግኝ ህብረተሰብን በማስተባበር መትከል
- በ 4 ከተሞች ላይ  የብስክሌት ትራንስፖርትን ማስፋፋት

## ግብ 5፡ የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት የዘርፉ ውጤታማነትን ማሳደግ

- በአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት የፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት 2000 ስልጠና መስጠት
- ከክልል እስከ መናኃሪያ ለሚገኙ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች፣ለማህበራት የቦርድ አመራር አካላት፣ ለዋና ሥራ አስኪያጆችና ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች፣የኦፕሬሽንና የአስተዳደር ሠራተኞች፤የተሽከርካሪዎች ባለሀብቶች፣ለአሽከርካሪዎች፣ለጫኝ አዉራጆች ለአስተባባሪዎች በጥቅሉ ለ 12041 በመመሪያዎች አፈፃፀምና በተክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና መስጠት፣
- ለ1000 በጭነት ትራንስፖርት ለፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች፤ለማህበራት ቦርድ አመራር አካላት፤ለዋና ስራ አስኪያጆችና ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች፤የኦፕሬሽን አስተዳደር ሰራተኞች ለባለ ተሽከርካሪ ባለሀብቶቸና አሽከርካሪዎች በጥናት በተለዩ ርዕሶች ላይ ስልጠና መስጠት
- በት/ቤቶች ውስጥ 700 የመንገድ ደህንነት ከበባትን ማጠናከርና 750 አዲስ ማቋቋም
- በቀበሌያት 660 የመንገድ ደህንነት ኮሚቴዎችን ማጠናከርና 360 አዲስ ማቋቋም፡
- ለ 500 የትምህርት ቤት የመንገድ ደህንነት ክበባት አስተባባሪ መምህራንና ር/ምህራን ማሰልጠ፤ለ 420 የቀበሌ የመንገድ ደህንነት ኮሚቴዎች ስልጠና መስጠት
- የመንገድ አጠቃቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ያገኘ ሰው 1,000,000 ከነበረበት ወደ 3,000,000 ማድረስ
- ለነባር አሽከርካሪዎች አደጋን ተከላክለዉ እንዲያሽከረክሩ የሚሰጠዉ ስልጠና ከ3600 በየአመቱ በ5% በማሳደግ ወደ 5400 ማድረስ
- ለ__________ መንገድ ደህንነት ባለሙያዎች ለ__________ትራፊክ ፖሊስ ተከታታይነት ያለዉ ስልጠና መስጠት

- 8 መናኽሪያዎችን በዋይድ ኤሪያ ኔት ወርክ ማገናኘትና የመረጃ አያያዝ፣ትንተናና ሥራጭት ዘዴውን ዘመናዊ ማድረግ፣
- የትራፊክ ቁጥጥሩን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለማገዝ በክልል ደረጃ 2 ተሽከርካሪና በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠም እና 10 በእጅ የሚያዝ የፍጥነት መቆጣጠሪያ (ራዳር) መግዛትና ማሰራጨት
- የወረዳዎችን የመንገድ ቁጥጥር ለማካሄድ የሚረዱ ሞተር ሳይክሎችን 1 ከነበረበት 20 ገዝቶ ማሰራጨት
- ለ 2400 የሴክተሩ፣ የዲስትሪክት፣ የዞንና የወረዳ ባለሙያዎች፣ የዲዛይን፣የግንባታ፣ የጥገና ማማከርና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን ለሚሰሩት ስልጠናዎችን መስጠት፣
- ለ 2840 የሴክተሩ ሰራተኞች በስርዓተ-ፆታ፣በኤች አይቪ እና ስነ -ምግባር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣
- የአዲስ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ግዥ በመፈፀም የማስፈፀም አቅማችን ማሳደግ
- የ10 ነባር አማከሪ እና ተቋራጭ ማህበራት ደረጃ ማሻሻል፣
- 50 አዲስ አማካሪና ተቋራጭ ማህበራትን ማደራጀትና ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ፣
- በትራንስፖርት ዘርፍ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በዓመት ይሰበሰብ የነበረውን ገቢ ከ________________ ብር ወደ________________ማድረስ
- በትራንስፖርት ዘርፍ ለዜጎች የተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል ከ__________ወደ_________ ማድረስ
- በመንገድ ዘርፍ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር አሁን ከነበረበት____________ ወደ__ ______ለማድረስ በመደበኛ የመንገድ ፕሮግራም ለ____________ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ለ________________ዜጎች የሥራ እድልን ማሳደግ፣
- አድስ ተሽከርካሪዎች ተቀብሎ የስምሪት ፍቃድ መስጠት ከ100 ወደ 1000 ማሳድገ

## ድርጊት መረሀ-ግብር

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | **ግብ 1:የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ** | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና መስጫ ትራፊክ ኮምፕሌክስ በ 2 ዞኖች ላይ መገንባት | ቁጥር | 0 | 1 | | | | | | | 1 | | |
| 1.2 | በ 4 ዞኖች የሚገኙ ጋራዦች በጥገና ወቅት የሚወጣውን አከባቢ በካይ ጋዝ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመከላከል እንዲቻል ጋራዦች በኢንደስትሪ ዞን ማደራጀት | ቁጥር | 0 | | 1 | | 1 | | 1 | | 1 | | |
| 1.3 | የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን በመገንባት አሁን ከነበረበት 19 ወደ 50 ማድረስ፣ | ቁጥር | 19 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 1.4 | 4 የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ከደረጃ 2 ወደ ደረጃ 1 ማሻሻል | ቁጥር | 0 | | 1 | | 1 | | 1 | | | 1 | |
| 1.5 | 22 የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 2 በማሻሻል ወደ 22 ማድረስ | ቁጥር | 22 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 1.6 | በከተሞች 40 የከተማ ታክሲ መናኸሪያዎች መለየትና 6 መገንባት፣ | መናኸሪያ ዎች መለየት በቁጥር | 0 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| | | መናኸሪያ ዎች መገንባት ቁጥር | 0 | | 1 | 1 | | 1 | | 1 | 1 | 1 | - |
| 1.7 | በ 10 ከተሞች ውስጥ የስምሪት መስመሮች ላይ የተሳፋሪ መጫኛና ማወረጃ ቦታዎችን በመለየት ከ 0 ወደ 200 ማድረስ፣ | ቁጥር | 0 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 |
| 1.8 | በከተሞች ውስጥ የስምሪት መስመሮች ላይ 110 ሼዶችን መገንባት | ቁጥር | 0 | 11 | 22 | 33 | 44 | 55 | 66 | 77 | 88 | 99 | 110 |
| 1.9 | 100 የመኪና ማቆሚያ ፓርኪንግ መገንባት | ቁጥር | 0 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 1.10 | 1 ቀላል የከተማ ባቡር መገንባት | ቁጥር | 0 | - | - | - | - | - | - | 1 | - | - | - |
| 1.11 | በ 4 ዋና ከተሞች ላያ የሳይክል መንገድ ለይቶ ተግባራዊ ማድረግ | ቁጥር | 0 | - | 1 | - | 1 | - | 1 | - | - | - | 1 |
| 1.12 | የጭነት ትራንስፖርት መናኸሪያ ግንባታ አሁን ካለበት ከ 0 ወደ 8 ማድረስ | በቁጥር | 0 | | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ<br>አፈፃፀ<br>ም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| ግብ 2፡ የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፣ | | | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | 1500 ጥራዝ ቦሎዎችን ማሳተምና ማሰራጨት፤ | ቦሎ በጥራዝ | | 150 | 150 | 150 | 150 | 150 | 150 | 150 | 150 | 150 | 150 |
| | 70000 ሰሌዳዎችን ማሳተምና ማሰራጨት | ሰሌዳ በቁጥር | | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 | 7000 |
| | 100000 የተሽከርካሪ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ ማሳተምና ማሰራጨት፤ | ሊብሬ በቁጥር | | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 1000<br>0 | 1000<br>0 |
| 2.2 | 100000 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ | በቁጥር | | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 10000 | 1000<br>0 | 1000<br>0 |
| 2.3 | 10000 ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳምኔትድ ማድረግና ማሰራጨት፤ | በቁጥር | | 2000 | 2000 | 2000 | 2000 | 2000 | | | | | |
| 2.4 | ክልሉን ከአጎራባች ክልሎች የሚያገናኘውን የስምሪት መስመር ቁጥር ከ__ወደ__ ማሳደግ፡ | ቁጥር | | | | | | | | | | | |
| 2.5 | የከተማና የገጠር የስምሪት መስመሮችን አሁን ከነበረበት___ ወደ_______ ማድረስ | ቁጥር | | | | | | | | | | | |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 2.6 | በክልሉ አሁን ላሉና ወደ ፊት ለሚከፈቱ የትራንስፖርት ስምሪት መስመሮች የጉዞ መስመሮችን የሚያሳይ 1 ካርታ /Route map/ማዘጋጀት፣ | ቁጥር | 0 | - | - | - | - | 1 | - | - | - | - | - |
| 2.7 | በክልሉ አሁን ያሉትን የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ከ8,00 ወደ ________ማድረስ፣ | ቁጥር | 800 | | | | | | | | | | |
| 2.8 | የተጓጓዘ ተሳፋሪ ቁጥር ከ 5,500,000 ወደ __13,750,000_ማድረስ፣ | ቁጥር | 53000000 | | | | | | | | | | |
| 2.9 | የሥምሪት ምልልስ ከ1,706,761 ወደ 1,731,761 በማድረስ የኪሎ ሜትር ሽፋን 32282684 ወደ837215146 ማድረስ | በኪ..ሜትር | 322,782,684 | 355060452 | 390567047 | 429623751 | 472586126 | 519844738 | 571829211 | 629012132 | 691913345 | 761104679 | 837215146 |
| 2.10 | የተጓጓዘ የከተማ ታክሲ ተሳፋሪ ቁጥር ………..ማድረስ | ቁጥር | | | | | | | | | | | |
| 2.11 | በክልሉ የህዝብ የንግድ ማመላለሻ የሚሰጡ ማህበራትን ቁጥር ከ 11 ወደ____ ማድረስ፣ | ቁጥር | 11 | | | | | | | | | | |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 2.12 | የመካከለኛ የህዝብ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያ ማስፋፋትን አሁን ከነበረበት 0 ናሙና ምርት ወደ 100 ማድረስ | ቁጥር | 0 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 2.13 | የከተማ ብዙሃን ትራንስፖርት የማጓጓዝ ድርሻ ከ2% ወደ 50% ማድረስ | ቁጥር | 2 | | | | | | | | | | |
| 2.14 | የከተማ ታክሲ ማህበራትን በማደራጀት ከነበረበት 77 ወደ 102 ማድረስ | ቁጥር | 77 | 79 | 81 | 83 | 85 | 87 | 90 | 93 | 96 | 99 | 102 |
| 2.15 | አማራጭ የከተማ ትራንስፖርትን ለማስፋፋት በ20 ከተሞች | የተስፋፋባቸው ከተሞች ቁጥር | 1 | 3 | 5 | 7 | 9 | 11 | 13 | 15 | 17 | 19 | 20 |
| | የከተማ አውቶቢስ፣ በ60 ከተሞች ሚኒ ባስና | የተስፋፋባቸው ከተሞች | 3 | 9 | 15 | 21 | 27 | 33 | 39 | 45 | 51 | 57 | 60 |
| | በ1 ከተማ ቀላል ባቡር ማስፋፋት ማእኪያ | የተስፋፋባቸው ከተሞች | - | - | - | 1 | - | - | - | - | - | - | - |
| 2.16 | የማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት በኤሌክትሪክ እና በታዳሽ ሀይል ድብልቅ የሚሰሩ አውቶብሶች 50 ወደ ሥራ ማስገባት | ቁጥር | - | | | | | | 50 | | | | |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 2.17 | በተለየ መስመር የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ተግባራዊ የተደረገባቸው ከ50 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች ብዛት ወደ 11 ማድረስ | ቁጥር | - | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 11 |
| 2.18 | በወንዞችና ሀይቆች ላይ የሚሰሩ ባለሞተር ጀልባ ኦፕሬተሮች አሁን ካለበት 16 ወደ 36 ማድረስ | ቁጥር | 16 | 18 | 20 | 22 | 24 | 26 | 28 | 30 | 32 | 24 | 36 |
| 2.19 | የፐብሊክ ሰርቪስ ትራስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት ወደ 100,000 ማድረስ | በቁጥር | - | | 10000 | 2000 | 30000 | 40000 | 50000 | 60000 | 70000 | 90000 | 100000 |
| 2.20 | የፐብሊክ ሰርቪስ አውቶቡስ አቅርቦት ብዛት ወደ 200 ማድረስ | በቁጥር | - | 20 | 40 | 60 | 80 | 100 | 120 | 140 | 160 | 180 | 200 |
| 2.21 | የገጠር መንገዶች መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋን በመቶኛ ከ70 ወደ 100 ማድረስ | በመቶኛ | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 | 95 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.22 | አዳዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን በማደራጀት ከነበረበት 10 ወደ 40 ማድረስ | ቁጥር | 40 | 42 | 44 | 46 | 48 | 50 | 52 | 54 | 56 | 58 | 60 |
| 2.23 | በጭነት ትራንስፖርት በድርጅት ወይም በኩባንያ ለሚደራጁ ባለሀብቶች የደረጃ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ 16 ከነበረበት ወደ 36 | ቁጥር | 16 | 18 | 20 | 22 | 24 | 26 | 28 | 30 | 32 | 34 | 36 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | ማሳደግ | | | | | | | | | | | | |
| 2.24 | የጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ደረጃ 574 ከነበረበት 5740 ማድረስ | ቁጥር | 1500 | 1700 | 1900 | 2100 | 2300 | 2500 | 2700 | 2900 | 3100 | 3300 | 3500 |
| 2.25 | በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ የግል ኦፕሬተሮች አደረጃጀት በጭነት አይነት /Specialization/ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን 2 ከነበረበት 12 ማድረስ፣ | ቁጥር | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| **ግብ 3፡ የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ** | | | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት የሚሰጡ ማሰልጠኛ ተቋማትን ድርሻ ከ65 ወደ 100 ማድረስ | በመቶኛ | 65 | 80 | 90 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 3.2 | በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የሚሰጡ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ድርሻ በመቶኛ ከ25 ወደ 100 ማድረስ | በመቶኛ | 25 | 75 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 3.3 | የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሽፋን በመቶኛ ከ50 ወደ 100 ማድረስ | በመቶኛ | 50 | 70 | 90 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 3.4 | 89 የነበረውን የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፈቃድ 119 ማድረስ | በቁጥር | 89 | 92 | 95 | 98 | 101 | 104 | 107 | 110 | 113 | 116 | 119 |
| 3.5 | አለም አቀፍ ደረጃ የጠበቁ የአሽከርካሪ ሞዴል ማሰልጠኛ ተቋማት ብዛት ወደ 5 ማሳደግ፣ | በቁጥር | 0 | 9 | 17 | 25 | 33 | 41 | 49 | 57 | 65 | 73 | 80 |
| 3.6 | በሲሙሌተር የተደገፈ የአሽከርካሪዎች እና የቴክኒሽያኖች የተግባር ስልጠና በመቶኛ 6 ከነበረበት 100 ማድረስ | በመቶኛ | 6 | 10 | 25 | 40 | 55 | 70 | 85 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 3.7 | 4 የነበረውን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ፈቃድ በመስጠት 14 ማድረስ | ብቁጥር | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 3.8 | 149 የነበረውን የተሽከርካሪ ጥገና መስጫ ጋራዦችን ፈቃድ ቁጥር 249 ማድረስ | ብቁጥር | 149 | 159 | 169 | 179 | 189 | 199 | 209 | 219 | 229 | 239 | 249 |
| 3.9 | 60000 ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ማድረግ | ብቁጥር | 50902 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 | 6000 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | ብቃታቸው የተረጋገጠ ተሽከርካሪዎችን መመዝገብ 132460 ከነበረበት ወደ 332460 ማድረስ | በተሽከርካሪ ቁጥር | 132460 | 152460 | 172460 | 192460 | 212460 | 232460 | 252460 | 272460 | 292460 | 312460 | 332460 |
| | የተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ 42420 ከነበረበት 110027 ማድረስ | በተሽከርካሪ ቁጥር | 42420 | 46662 | 51328 | 56461 | 62107 | 68318 | 75150 | 82665 | 90931 | 100024 | 110027 |
| | ብቃታቸው የተረጋገጠ አሽከርካሪዎች ከ160000 ከነበረበት ወደ 420000 ማድረስ | በተሽከርካሪ ቁጥር | 160000 | 186000 | 212000 | 238000 | 264000 | 290000 | 316000 | 342000 | 368000 | 394000 | 420000 |
| 3.10 | 1320 የትራፊክ አደጋ አሁን ከነበረበት በ5% በየዓመቱ በመቀነስ በ2022 ወደ 789 ማድረስ፤ | ቁጥር | 1320 | 1254 | 1191 | 1131 | 1074 | 1020 | 969 | 921 | 875 | 831 | 789 |
| 3.11 | ሞት የሚያስከትል አደጋ ከ594 በ5% በመቀነስ ወደ 355 ማድረስ | ቁጥር | 594 | 564 | 536 | 509 | 484 | 460 | 437 | 415 | 394 | 374 | 355 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 3.12 | የንብረት ዉድመት ከብር 30,600,469 በ5% በመቀነስ ወደ ብር 18,321,632 ማድረስ | ቁጥር | 30,600,469 | 29,070,446 | 27,616,924 | 26,236,078 | 24,924,274 | 23,678,060 | 22,494,157 | 21,369,449 | 20,300,977 | 19,285,928 | 18,321,632 |
| 3.13 | በሰው ሂይወት ላይ በአስር ሺህ ተሽከርካሪ ይደርስ የነበረውን 48 ሞት ወደ 10 ማድረስ | ብቁጥር | 48 | **44** | 40 | 36 | 32 | 28 | 24 | 20 | 16 | 13 | 10 |
| 1.14 | የደህንነት ቀበቶ (safety belt) ገጥመዉ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር በየአመቱ በ30% በማሳደግ 100% ማድረስ | በ መቶኛ | 0 | 30 | 60 | 90 | 100 | | | | | | |
| 3.15 | የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የገጠሙ የንግድ ተሽከርካሪዎች ቁጥር በየአመቱ በ20% በማሳደግ 100% ማድረስ | በመቶኛ | 0 | 20 | 40 | 60 | 80 | 100 | | | | | |
| 3.16 | 1500 አለም አቀፍ ምልክቶችን፣ | አለም አቀፍ ምልክት | 3646 | 3796 | 3946 | 4096 | 4246 | 4396 | 4546 | 4696 | 4846 | 4996 | 5146 |
| | 100 የማስጠንቀቂያ ማብራት፣ | የማስጠንቀቂያ መብርሀት | 25 | 45 | | 65 | | 85 | | 105 | | 125 | |
| | 4000 ገላጭ ጽሁፎችን | ገላጭ ጽሁፎ በቁጥር | 2000 | 2400 | 2800 | 3200 | 3600 | 4000 | 4400 | 4800 | 5200 | 5600 | 6000 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | 8000 የእግረኛ ማቋረጫ /ዜብራ ቅብ እና | ዜብራ በቁጥር | 2500 | 800 | 800 | 800 | 800 | 800 | 800 | 800 | 800 | 800 | 800 |
| | 600 የፍጥነት መገደቢይ | የፍጥነት መገደቢያ በቁጥር | - | 100 | 200 | 300 | | 400 | | 500 | 600 | | |
| 3.17 | የአህያ ወይም የፈረስ ጋሪ አንፀባራቂ አሁን ከነበረበት 26000 ወደ 106,000 ማድረስ | አንፀባራቂ በቁጥር | 26000 | 34000 | 42000 | 50000 | 58000 | 66000 | 74000 | 82000 | 90000 | 98000 | 106000 |
| 3.19 | የትራንስፖርት ዘርፍ ህጎች አፈፃፀም በመቶኛ ከ50% ወደ 100% ማድረስ | በመቶኛ | 50 | 75 | 85 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **ግብ 4፡ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሰረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ** | | | | | | | | | | | | | |
| 4.1 | 1000000 ችግኝ ህብረተሰብን በማስተባበር መትከል | በቁጥር | 0 | 100000 | 200000 | 300000 | 400000 | 500000 | 600000 | 700000 | 800000 | 900000 | 1000000 |
| 4.2 | በ10 ከተሞች ላይ የብስክሌት ትራንስፖርትን ማስፋፋት | በቁጥር | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| **ግብ 5፡ የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት የዘርፉ ውጤታማነትን ማሳደግ** | | | | | | | | | | | | | |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ከማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት የፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት 6200 ስልጠና መስጠት | በቁጥር | | 620 | 620 | 620 | 620 | 620 | 620 | 620 | 620 | 620 | 620 |
| | ለማህበራት የተሽከርካሪዎች ባለሀብቶች፣ ለአሽከርካሪዎች፣ለጫኚ አዉራጆች ለአስተናባሪዎች በጥቅሉ ለ60,800 አፈፃፀምዎችና ፈፃሚዎች ስልጠና መስጠት፣ | ቁጥር | 21,203 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 | 6080 |
| | ለ5000 በጭነት ትራንስፖርት ከክልል እስከ ታችኛው መዋቅር ለፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች ፤ለማህበራት ለባለ ተሽከርካሪ ባለሀብቶችና አሽከርካሪዎች ስልጠና መስጠት | በቁጥር | | 500 | 500 | 500 | 500 | 500 | 500 | 500 | 500 | 500 | 500 |
| | በት/ቤቶች ውስጥ 4659 የመንገድ ደህንነት ክበባትን ማጠናከር | በቁጥር | | 466 | 466 | 466 | 466 | 466 | 466 | 466 | 465 | 466 | 466 |
| | 2500 አዲስ መቋቋም | በቁጥር | | 250 | 250 | 250 | 250 | 250 | 250 | 250 | 250 | 250 | 250 |
| | በቀበሌያት 4850 የመንገድ ደህንነት ኮሚቴዎችን ማጠናከርና | ማጠናከር በቁጥር | | 485 | 485 | 485 | 485 | 485 | 485 | 485 | 485 | 485 | 485 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | 2000 አዲስ ማቋቋም፡ | ማቋቋም በቁጥር | | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 |
| | ለ3838 የትምህርት ቤት የመንገድ ደህንነት ክበባት አስተባባሪ መምህራንን እና ር/ምህራንን ማሰልጠ፤ | በቁጥር | | 380 | 380 | 380 | 380 | 380 | 380 | 380 | 380 | 380 | 3838 |
| | ለ4040 የቀበሌ የመንገድ ደህንነት ኮሚቴዎችን ስልጠና መስጠት | በቁጥር | - | 404 | 404 | 404 | 404 | 404 | 404 | 404 | 404 | 404 | 404 |
| | የመንገድ አጠቃቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህረት ያገኘ ህብረተሰቡ ቁጥር5,000,000 በየአመቱ በ100,000 በማሳደግ ወደ 6,000,000 ማድረስ | በቁጥር | - | 5,100,000 | 5,200,000 | 5,300,000 | 5,400,000 | 5,500,000 | 5,600,000 | 5,700,000 | 5,800,000 | 6,900,000 | 6,000,000 |
| | ነባር አሽከርካሪዎችን ስልጠና ከ42,000 በየአመቱ በ5%ማሳደግ ወደ 60,000 ማድረስ | በቁጥር | 42,000 | 42,000 | 44,100 | 46,305 | 48,620 | 51,005 1 | 53,603 | 56,283 | 59,097 | 60,000 | 60,000 |
| | ለ3680 መንገድ ደህንነት ባለሙያዎች | በቁጥር | 3680 | 368 | 368 | 370 | 368 | 368 | 368 | 368 | 368 | 368 | 368 |
| | ለ2000 ትራፊክ ፖሊስ ተከታታይነት ያለዉ ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 2000 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 | 200 |
| | 161 መናኸሪያዎችን በዋይድ ኤሪያ ኔት ወርክ ማገናኘትና የመረጃ አያያዝና | በቁጥር | 0 | | | 130 | 161 | | | | | | 161 |

| ተቁ | ግብ እና ተግባራት | መለኪያ | የሚደረስበት ትንበያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ አፈፃፀም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | ሥርጭትን ማዘመን | | | | | | | | | | | | |
| | የትራፊክ ቁጥጥሩን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለማገዝ በክልል ደረጃ 2 ተሽከርካሪና በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠም | በቁጥር | 0 | | 1 | | 2 | | | | | | |
| | 25 በእጅ የሚያዝ የፍጥነት መቆጣጠሪያ (ራዳር) እንዲገዛና እንዲሰራጭ ማድረግ | በቁጥር | 0 | | 5 | | 10 | | 15 | | 20 | | 25 |
| | በትራንስፖርት ዘርፍ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በዓመት ይሰበሰብ የነበረውን ገቢ ከ158,620,000ብር ወደ 1,614,160,000 ማድረስ | የተሰበሰበ ገቢ በብር | 158,620,000 | | | | | | | | | | 1,614,160,000 |
| | በትራንስፖርት ዘርፍ ለዜጎች የተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል ከ47,521 ወደ 76,032ማድረስ | ይተፈጠረ የሥራ ዕድል በቁጥር | 47,521 | | | | | | | | | | 76,032 |

## የማስፈፀሚያ ተቋማዊ አቅም፣ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች

- የሞተር አልባ IMt አፈፃፀም መመሪያ
- የብዙሃን ትራንስፖርት ማስፋፊያ ስትራቴጂ
- የትራፊክ ፍሰት ቁጥጥር ስትራቴጂ
- ፐብሊክ ትራንስፖርት ደንብ
- የዘርፉን የአደረጃጀት ማሻሻያዎች
- የወራዊ ድርጊት መረሃ-ግብርና መናኸሪያ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ ማሻሻል
- የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መመሪያ

## ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍቻ መንገዶች

### ችግሮች/ስጋቶች/

በሚቀጥለው 2013-2022 የአስር አመት የልማት መሪ እቅድ ሊተገበሩ የታሰቡ ዕቅዶችን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ፈታኝ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዩች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ለዘርፉ የሚመደበው በጀት በተጣለው ግብ ልክ ካልሆነየዕቅዱን ተግባራዊነትን ሊያጓትት ይችላል፣
- በክልል ደረጃ የሚደረጉ የመዋቅር አደረጃጀት ለውጦች በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችልመሆኑ፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በተገቢው ደረጃ ተቀናጅቶ የመስራት ባህሉ የዳበረ አለመሆን፣
- የማስፈፀም አቅም ውስንነትና ቁርጠኝነት ማነስ፣
- የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ለመቅረፍ በሚደረገው ትግል ሊያጋጥም የሚችል ፈተና መኖር፣

## 8.2 የመፍትሔ አቅጣጫዎች

ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና እና ሌሎች ችግሮች ቢከሰቱና የሁኔታዎች መለዋወጥ ቢያጋጥም የዕቅድ ዘመኑ አፈፃፀም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ እነዚህን ችግሮች ትርጉም ባለው መልኩ በወቅቱ በመፍታት ሊያሳድሩ የሚችሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- የፋይናንስ አቅርቦት (በጀት) በተመለከተ የክልሉን ፋይ/ኢኮ/ልማት ቢሮ እና የክልሉን መንግስት ስለ ፕሮጀክቶቹ ምንነትና ፋይዳ በማስረዳት የትራንስፖርት ዘርፉ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ፣
- ከባለድርሻ አካለት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ባህል ማዳበርና በጋራ ዕቅድ መመራት
- ተከታታይነት ያለው ሥልጠና በመስጠት የአቅም ውስንነት ችግሮችን መቅረፍ፣

## 4. የሰው ሃብት ፍላጎት

በአሁኑ ወቅት በትራንስፖርት ሴክተር ከክልል እስከ መናኸሪያ ድረስ በስራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው የሰው ኃይል ------ ሲሆን፤ ይህንን የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ለማሳካት እንዲቻል የሚያስፈልገው አጠቃላይ የሰው ኃይል --------- ይደርሳል፡፡ ዝርዝር የሰው ሃይል ፍላጎቱን በትምህርት ደረጃ እና በዓይነት በሚያሳይ መልኩ ከዚህ ዕቅድ ጋር በዕዝል ----- አባሪ ተደርጓል፡፡

## 5. የፋይናንስ ፍላጎት

የአስር ዓመት መሪ ዕቅዱን ለማሳካት እንዲቻል የሚያስፈልገዉ ወጪ ከመንግስት በቀጥታ የሚመደብ ብር 35,285,777 ከነበረበት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች 100,000,000 ከመንግስት በቀጥታ ብር 1,247,645,787.0 እና በድምሩ ብር 1,347,645,787.0 በሥራ ላይ ይውላል፡፡

## 6. የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት

### 6.1 ድጋፍና ክትትል አግባቢ

የታቀዱ ስራዎች በተያዘላቸው መርሃ ግብር መሰረት እየተከናወኑ መሆኑን ለመከታተል፣እና በትግበራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት ወቅታዊ ድጋፍና ማስተካከያ ለማድረግ ይህ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተቀምጧል፡፡

የክትትል ሥራ በየደረጃው የተለያዩ ዘዴዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን፤ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ መንገዶች

- ከ2013 ዓ.ም. መግቢያ ጀምረው በቢሮ፤በዞንና ወረዳ ደረጃ ለ10 ተከታታይ ቀናት ያለፈው በጀት ዓመት አፈፃፀም መገምገምና ከተቋም እስከ ግሌሰብ ፈፃሚ ድረስ ጠንካራና ደካማ አፈፃፀም በመገምገም ለቀጣይ ሥራ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- የፈፃሚዎችና ዳይሬክተሮችን ውጤት መሙላት፤የግብ ሥምምነት ማዘጋጀት፤ የአገልግሎት መስጫ ቅጾችና መዝገቦችን ማዘጋጀት፤የአገልግሎት ስታንዳርዶችን ማዘጋጀትና ለባለጉዳይ መለጠፍ፤ኮምፒዩተሮችና ላፕቶፖችን መጠገንና የሥራ አከባቢውን ውበትና ንጽህና የመሳሰሉትን ሥራዎች ማከናወን፡፡
- ከቀን 11 ጀምሮ እስከ 20 ድረስ ባሉት ቀናቶች በማኔጅሜንት የሚመራ ቡድን ሁሉንም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎችን በአካል በመገኘት ለቀጣይ በጀት ዓመት ሥራ ዝግጁ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ

- በየሳምንቱ በወረዳና መናኸሪያ ደረጃ የተሰሩትን የዕቅድ አፈፃፀሞችን ለዞን ማዕከል፤ በየ15ቀኑ ዞኖች ለክልል የሚያስተላልፉ ሲሆን በየወሩ በክልል ደረጃ ከየዳይሬክቶሬቶች የሚቀርቡ አፈጻጸም ሪፖርቶች በማኔጅሜንት ደረጃ ተገምግሞ ለሥራ ክፍሎች ግብረ-መልስ መስጠት

- በየ3 ወሩ ከ15-25 ድረስ ባሉት ወቅት በማኔጅሜንት የሚመራ ቡድን ሁሉንም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎችን በአካል በመገኘት በወረቀት ላይ የነበሩ ሥራዎች በመረት ላይ ተመሳሳይ መሆናቸውን በማረጋገጥና ግምገማ ካደረገ በኃላ ግብረ-መልስ መስጠትና በተዋረድ ባለው በአፈፃፀም ላይ ክፍተት ካለ ልዩ ድጋፍ ማድረግና ብሎም የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ለመንግስት ግብረ-መልስ መስጠት

## የትራንስፖርት ዘርፍ የሠው ኃይል ፍላጎት በትምህርት ደረጃ

| የትምህርት ደረጃ | መነሻ ዓመት (Stock) | ትንበያ | | | | | | | | | | የ10 ዓመት ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| 12 ያጠናቀቀ/ች እና ከዚያ በታች | | | | | | | | | | | | |
| በቴክኒክና ሙያ የተመረቀ/ች | | | | | | | | | | | | |
| ኮሌጅ ዲፕሎማ | | | | | | | | | | | | |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | | | | | | | | | | | | |
| የማስተርስ ዲግሪ | | | | | | | | | | | | |
| ፒኤችዲ (ዶክትሬት ዲግሪ) | | | | | | | | | | | | |
| ጠቅላላ ድምር | | | | | | | | | | | | |

## በልማት ፕላኑ ዘመን የትራንስፖርት ዘርፍ የፋይናንስ ፍላጎትና ምንጭ (በሚሊዮን ብር)

| ተ.ቁ | ዝርዝር | መነሻ ዓመት 2012 | ትንበያ | | | | | | | | | | የ10 ዓመት ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| 1. | ጠቅላላ ወጪ | | 84,054,354.00 | 172,329,790.00 | 116,332,769.00 | 127,586,045.00 | 147,114,649.00 | 157,946,113.00 | 154,110,724.00 | 158,141,796.00 | 62,575,975.00 | 67,453,572.00 | 1,247,645,787.0 |
| 1.1 | የካፒታል ወጭ | 16600000 | 61,300,000.00 | 147,300,000.00 | 88,800,000.00 | 97,300,000.00 | 113,800,000.00 | 121,300,000.00 | 113,800,000.00 | 113,800,000.00 | 13800000 | 13800000 | 885,000,000.00 |
| 1.2 | የመደበኛ ወጭ | 18685777 | 22754354 | 25029790 | 27532769 | 30286045 | 33314649 | 36646113 | 40310724 | 44341796 | 48775975 | 53653572 | 7 |
| 3. | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | ከመንግስት በጀት | 35285777 | 84,054,354.00 | 172,329,790.00 | 116,332,769.00 | 127,586,045.00 | 147,114,649.00 | 157,946,113.00 | 154,110,724.00 | 158,141,796.00 | 62,575,975.00 | 67,453,572.00 | 0 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በትራንስፖርት ዘርፍ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በዓመት ይሰበሰብ የነበረውን ገቢ ከ158,620,000ብር ወደ 1,614,160,000 ማድረስ | የተሰበሰበ ገቢ በብር | | 32000 | 37000 | 39000 | 41000 | 46000 | 48000 | 50000 | 52000 | 54000 | 56000 |
| | በትራንስፖርት ዘርፍ ለዜጎች የተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል ከ47,521 ወደ 76,032ማድረስ | ይተፈጠረ የሥራ ዕድል በቁጥር | 6 | | 3 | | | 3 | | | | | |